## ኢትዮሚድያ ርእሰ አንቀጽ

# የሕዝብን ድምፅ ስሙ!

**ትርጉም አላና አብሴ**

*"የሕዝብ ድምጽ የእግዚአብሄር ድምጽ ነው"ይላል የጥንቱ አባባል። ነገር ግን ለአለፉት ብዙ አመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ ታፍኗል። ዛሬ በኢትዮጵያ መናገር በመንግሥት የሚያስጠይቅ ታላቅ ወንጀል ነው። ማለትም እውነቱን መናገር ስለሙስና ፤ስለአባገነናዊ አስተዳደርና ስለፍትህ መጥፋት መናገር ፤መጻፍም እንዲሁ ይህም እውነትን መዘገብ፤ የባለስልጣኖችን ምግባረ ብልሹነትና በስልጣን የመባለግ ማስረጃዎችን በፅሁፍ ማውጣት፤ የመንግስት ባለስልጣናትን ተጠያቂ ሊያደርጉ የሚችሉ ቁልፍ መረጃዎችን ተከታትሎ መፃፍና ማጋለጥ እጅግ የከፋ ኃጢያት ነው። በዚህም የተነሳ ጋዜጠኞች፤ ዜና ዘጋቢዎችና አሳታሚዎች በሀገር ጠላትነት ተፈርጀው ተከሰዋል። ዛሬ ሙሰኞችንና በስልጣን የባለጉ ባለስልጣናትን ከተጠያቂነት ለማዳንና የወንጀለኝነታቸውን መረጃዎች ደብዛ ለማጥፋት የብረት መጋረጃ በመላ ሀገሪቱ ተዘርግቷል።*

*በ1997 ከተደረገው ምርጫ ጀምሮ በርካታ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኞች ታስረዋል፤ ብዙዎችም ሀገር ለቀው እንዲሰደዱ ተገደዋል። አገዛዙ ማንኛውንም የፅሑፍና የኤሌክትሮኒክስ የዜና አውታሮችን በብቸኝነት ተቆጣጥሯል። በርካታ የግል ጋዜጦች ተዘግተዋል። አሳታሚዎች ሆን ተብሎ እንዲከስሩም ተገደዋል ወይም እንዳይነቀሳቀሱ ታግደዋል።*

*ኢትዮጵያ ውስጥ በነፃው ፕሬስ ላይ በተደጋጋሚ የሚሰነዘረው ጥቃት ቅጥ ያጣ ነው። አገዛዙ የተቃዋሚ ድምፆችንና አማራጭ የዜና አውታሮችን ማገድ አልበቃ ብሎት ነፃ ጋዜጦችን እረግጦ ለመቆጣጠር እንዲያመቸው ያወጣቸውን ሕጎች መተላለፍ የሚያደርስባቸውን መከራ እያወቁና ለሚደረግባቸው ጥብቅ የሕትመት ቁጥጥር አሜን ብለው ለመገዛት ፈቃደኛ ለሆኑ ጋዜጠኞች ሳይቀር ያንን ጫና አብዝቶ በማያፈናፍን ሕግና ደንብ የሰነገውን የሕትመት ፈቃድ ተብዬ እንኳን ከልክሏቸዋል።*

*አገዛዙ የሃገር ውስጥ ፅሑፎችን መቆጣጠር አልበቃ ብሎት ዓለም አቀፍ የዜና ምንጮችንና ጋዜጠኞችን ሳይቀር ማገድ ስራዬ ብሎ ተያይዞታል። ባለፈው ዓመት የኒውዩርክ ታይምስን ዘጋቢዎች በመሳሪያ አስፈራርቷል። የእነርሱን መሰል የዋሺንግተን ፖስትና የቢቢሲ ጋዜጠኞችን በማዋከብ በክልሉ በሙያቸው እንዳይንቀሳቀሱ በማገድ ወይም መንግስት በሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን የመብት ረገጣ አስመልክቶ ባቀረቡት ዘገባ ምክንያት ወደፊትም እንዳይዘግቡ በማገድ ከሃገር እንዲባረሩ አድርጓል። ከኔ አልወገኑም ያላቸውን ድህረ ገፆችም አግዷል። በቅርቡም እንደ አሜሪካ ድምፅ፤የጀርመን ዶች ቬሌ የመሳሰሉት ራዲዮ እወጃዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዳይሰራጩ የአየር ሞገዳቸውን በማወክ ላይ ነው።*

*ለመሆኑ አገዛዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም እንዳይሰማና ነገሮች ሁሉ ከሕዝብ እንዲደበቁ ለምን እንደዚህ ይዋትታል? እውን ዓለም ሁሉ ስለ እነርሱ ሥራ እየዋሸና እነርሱ ብቻ እውነቱን ስለሚናገሩ ይሆን? ወይስ እውነቱን መሸከም ስለከበዳቸውና እነርሱን የተቃወመ ሁሉ መታፈን ስላለበት?*

*አገዛዙ ዕውነቱን መሸከም እንደከበደው ግልፅ ነው። ሀቁ ለማንም ወለል ብሎ ይታያል። በሕጋዊ የፓለቲካ ተቃዋሚዎችና ከአስተዳደሩ ጋር ባልተስማሙ ወገኖች ላይ በጅምላ የሚደረገው ጭቆና፤ ጋዜጠኞችን ወህኒ ቤት በማጎር ሀቁን መደበቅ አይችልም። ምንም ያህል የዲፕሎማቲክ አቲሆ ባቲሆ ዝባብንኬ የአገዛዙን ክፋት ሊሸፍን አይችልም። የኢትዮጵያ ገዥዎች በዓለም ላይ በክፉ ምግባራቸው እጅግ በጣም ከታወቁት መንግስታት ሁሉ የከፉ የመሆኑን ዕውነታ አይለውጠውም። በሀሰት የተቀመሩ የምጣኔ ዕድገት አመልካች አሀዞች የሕዝቡን የዕለት ተዕለት የስቃይ ኑሮ አይደብቁትም። በግልፅ*

የሚታየው ነገር የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሕይወቱ መሰረታዊ ፍላጎቶቹን ሊያሟሉለት የሚችሉትን እንደ ጤፍ በርበሬና ጨው የመሳሰሉትን የመግዛት ዓቅም አጥቷል። በመሰረታዊ የጤና አገልግሎት እጦት፤ የኤይድስ ህሙማን መብዛት፤በሀገሪቱ ላይ እያንዣበበ ያለው የድርቅና የሚያስከትለው ሰፊ የረሀብ አደጋ (ይህ በደቡብ ክልል በአሁኑ ሰዓት በገሃድ እየታየ ያለ ነገር ነው )፤ ደካማ የትምህርት መዋቅር፤ የወጣቱ በአብዛኛው ሥራ አጥ መሆን እና ሌሎች ሕብረተሰባዊና ኢኮኖሚያዊ እውነታዎችን አተኩረው የሚከታተሉትን የነፃ ፕሬሶችን ዓይን በማወር ከአለም መሰወር አይቻልም። በዚህም በዚያም ጉዳዩን ለመሸፋፈን ቢሞከርም በአንድ በትንሽ ቡድን ውስጥ ያሉ ግለሰቦች በሀብት የተንበሸበሹ፤ የናጠጡ ሀብታሞች መሆናቸው ለማንም ወለል ብሎ የሚታይ ሀቅ ነው። ለአገዛዙ ያደገደጉ ሆዳሞችም ዋና ዋና የሚባሉ የኢካኖሚ ክፍሎችን አግበስብሰው አንቀው ስለመያዛቸው ሀገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ ነው።

ዕውነቱ እንዲህ ፍጥጥ ብሎ የማይካድ ከሆነ ጭቆናው ለምን እንዲህ ከፋ? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የመረጃን ሥራ ቁጥጥር ባሕሪይ መመርመር የግድ ነው። ተቃዋሚዎችን መጨቆን፤ ነፃውን ፕሬስ ማዋከብ የሁሉም አምባገነኖች የወል ባሕሪይ ነው። በናዚ ዘመን የፕሮፓጋንዳ ሚኒስቴር የነበረው ጆሴፍ ጎብላ በአንድ ወቅት እንደተረዳው መንግስቱ ተቃዎሚ ድምፆችን ሁሉ ዘግቶ የራሱን የሀሰት ፕሬፓጋንዳ በተደጋጋሚ በመንዛት ሕዝቡ ይህንን ከማመን ውጪ ምንም አማራጭ የለውም ይል ነበር። ይህንን የውሸት አስተሳሰብ የኢትዮጵያ መንግስት ገዥዎችም በስራ ላይ በመተግበር ላይ ናቸው። ተቃዋሚ ኃይሎችንና የተለየ አመለካከት ያላቸውን መጨፍለቅ፤ ነፃ ጋዜጦችን ማገድ፤ ከጊዜ ብዛትና በድግግሞሽ ሕዝቡ የኢህአዴግ መንግስት የሚያናፍሰውን የሀሰት ወሬ እውነት ነው ብሎ ከመቀበል ውጪ ምርጫ ማሳጣት ዘዴ ብሎ ይዞታል። በዓለም አቀፍ መንደር ሀሰተኞች ፤ ውሸትና ውሸታሞች የመደበቂያ ስፍራ የላቸውም። መረጃዎችን ለመከተር የተዘረጋው የብረት መጋረጃ ምንም ጥቅጥቅ ያለ ቢሆንም ሀቁንና ወቅቱ የወለደውን ሀሳብ ገትቶ መያዝ አይችልም።

አገዛዙ ነፃ ጋዜጠኞችን ከሙያቸው በማሰናከልና እስር ቤት በመወርወር፤ የሙያ ፈቃድ በመከልከል በሀሰት ክስ ከፍቶ በማዋከብ ሀቁን ከሕዝብ መደበቅ ይቻላል ብሎ ያምናል። ይህ ግን እራስን ማሞኘት ነው። ምንም እንኳን የሀገሪቱ ነፃ ጋዜጦች ቢታፈኑም ጥቂት ጋዜጠኞች ዘጋቢዎችና አሳታሚዎች እውነቱ ታፍኖ እንዳይቀር ትግሉን ተያይዘውታል። በውጭ የሚኖሩ ታታሪ የድህረ ገድ አዘጋጆች፤ ብሎገሮች የሬዲዩ፤ የቴሌቪዥንና የመወያያ መድረክ አስተናጋጆችና አስተያየት ሰጪዎች አገዛዙ በህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን በደል ለዓለም ለማሳወቅ ሌት ተቀን እየጣሩ ነው። እነዚህ ጭቆናን አሻፈረኝ ያሉ የሕዝብ ድምፆች ናቸው። የሕዝቡን ስቃይ በደሉንና እሮሮውን ያስተጋባሉ። በእርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትንፍሽ እንዳይል በኃይል ታግቷል። ሆኖም ግን ልሳን አልባ አይደለም።

አገዛዙ ጥቂቶችን ሰዎችን ለሁል ጊዜ ማፈን ይችል ይሆናል፤ አንዳአንድ ጊዜ ደግሞ ሁሉንም ሰው ለተወሰነ ጊዜ ማፈን ይችል ይሆናል፤ ግን ሁሉንም ሰው ለሁል ጊዜ ፀጥ ማድረግ ግን አይችልም። የሕዝብ ድምፅ የእግዚይሔር ድምፅ ነው ብለን በእውነት እናምናለን። ሕዝብም ሆነ እውነትንም ለዘላለም ፀጥ ማድረግ አይቻልም።

ገጣሚው ጀምስ ሩዘል ሎዌል እንዳለው፤

ውሸታም ሁል ጊዜ በዙፋን ላይ ይጠለጠላል፤
የእውነት መሰላል የውሸትን ዙፋን ይንጠዋል፤
እውነትን የያዘ መሰረተ ጠንካራ ይሆናል፤
ከደብዛዛው ብርሀን ጥላ ስር አምላክ በጀርባው ይቆማል፤
እርሱንም ይጠብቀዋል፤